ኪንግደም ሳውድ ዐረቢያ
በእስልምና ጉዳዮች፣ ገንዘብ ስጦታ፣
ዳእዋና መምሪያ ሚንስቴር
የህትመትና ሳንሳዊ ምርም ድርጅት

# የሐጅ ጉዞ የጀመረ ሰው ወደ ሚቃት «የኢሕራም ቦታ» ሲደርስ ሊከተላቸው የሚገባው ደንቦች

አዘጋጅ

አብደረዛቅ ቢን አብደልሙሕሲን
አልበድር

آداب الحاج عند الوصول إلى الميقات باللغة الأمهرية

በአላህ ስም እጅግ በጣም አዛኝ በጣም ርህሩህ በሆነው።

ምስጋና ለዓላማቱ ጌታ ላአላህ ይገባው። የአላህ አክብሮት እዝነትና የማክበር ሰላምታ የመልእክተኞቹ ሁሉ ሊቅ በሆኑት በነብያችን ሙሀሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይሁን። ከዚህም በኋላ…

-የሐጅን ሥራ የጀመርክ ወንዲሜ ሆይ!- ይህን ታለቅ የአላህ ትእዛዝና የተከበረ ዒባዳ፣ በበይቱላህ አልሐራም ሐጅ ማድረግን ለመፈጸም መነሳትን በማቅለል አላህ ስለአከበረህ እንኳን ደስ ያለህ አልሃለሁ።

እነሆ አሁን አንተ ወደ ጥንታዊው የአላህ ቤት ለምታደርገው ታላቅ

ጉዞና የተከበረው መንገድ የረዥም ጉዞ መጀመሪያና መፈትለኪያ ከሆነው «ሚቃት» የኢሕራም መያዣ ቦታ ደርሰሃል፡፡ ይህን መንገድህን ቀኝበቀኝ እንዲያደርግለህ፣ በተገዢነት የምታደርሰውን ትእዛዝ እንዲቀበልህና ቀጥተኛውን መንገድ እንዲመራህ አላህን እንለምናለን፡፡

-የሐጅን ሥራ የጀመርክ ወንዲሜ ሆይ!- በዚህ አጋጣሚ በዚህ በ«ሚቃት»ኢሕራም መያዣ ቦታ በምትቆይበት ጊዜ ልታስታውሳቸው ስለሚገባ ጥቂት አሳሳቢ ነገሮች ላስታውስህ እወዳለሁ፡፡

1. የሐጅን ሥራ የጀመርክ ወንዲሜ ሆይ- ይህን የሐጅ ሥራህን የምትጀምረው ለወንጀልህና ኃጢ

ያትህ ሁሉ ንጹህ የሆነን ጸጸት«ተውባ» ወደ አላህ በመጸጸት «መቶበት» መሆን አለበት።

2. በሐጅና በኡምራ ሥራህ የአላህን ውዴታ፣ የመጨረሻውን ቀን ምንዳና እሱ በሚወዳቸው መልካም ቃላትና በጎ ሥራዎች ወደሱ መቃረብን ኢላማ ማድረግ ይጠበቅብሃል።
3. የሐጅን ሥራ የጀመርክ ወንዲሜ ሆይ!- በሐጅና በኡምራ ሥራህ ሁሉ ቅንና ብሩህ በሆነው መንገድ እንዲትጓዝና ሐጅህን ለሚያበላሹ ወይም ምንዳውን ለሚቀንሱ ነገሮች እንዳትጋለጥ በዚህ በሥራህ ጊዜ በሸሪኣው ደንብ

የሚፈቀድልህን ነገር ማወቅ ይኖርብሃል::

4 በተቻለህ መጠን ጊዜህን ሁሉ በዚክር፣ በዱኣ፣ ቁርአን በመቅራት፣ ጠቃሚ ካሴቶችን በማዳመጥና ፋይዳ ያላቸውን መጽሐፎች በማንበብ አሳልፍ::

5 -የሐጅን ሥራ የጀመርክ ወንዲሜ ሆይ! - የሐጅን ሥራ ከመጀመርህ በፊት መታጠብ፣ ሽቶ መቀባት፣ ሪዝህን -የላኛው ከንፈር ጠጉር- ማሳጠር፣ ጥፍሮችህን መቁረጥ፣ ከጉያህንና ከብብትህን መቀነስ ያለበትን መቀነስ ይወደድልሃል:: ጢምን መላጨት ግን በጥብቅ የተከለከለ ነው::

6 ወንድ ነጹህና ነጫጭ የሆኑ ሽርጥና ኩታ ለብሶ ቢሐርም ይወደዳል፡፡ ሴት ደግሞ ካሸበረቀ ልብስ በመራቅ የፈለገችውን ልብስ ለብሳ መሐረም ትችላለች፡፡

7 ቀኝ እጅን ማውጣት ሱና የሚሆነው በጡዋፍ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም በማንኛውም የኢሕራም ጊዜህ ትከሻህ እንደተሸፈነ መቆየት ሲኖርበት -በመግቢያም ሆነ በኡምራ ጡዋፍ- ብቻ እጅህን ማውጣት ትችላለህ፡፡

8 በኢሕራም ጊዜ ሣዓት፣ ቀለበት፣ መነጽር፣ ቀበቶና የተሰፋም «የተሸፈነም» እንኳን ቢሆን ጫማዎችን መልበስ ይፈቀዳል፡፡ ጃን ጥላ መያዝም ችግር የለበትም፡፡

9 ሐጅ የሐረመ ወንድ ሱሪ፣ ከናቴራ፣ ጀላብያ፣ ኮፊያ፣ ጥምጣምና ሽሚዝ «በአጠቃላይ የተሰፋ ልብስ» መልበስ አይፈቀድለትም፡፡

10 ሐጅ የሐረመች ሴት ኒቃብ«ዓይን ርግብ»ና የእጅ ጓንት መልበስ አይፈቀድላትም፣ ነገር ግን በኢሕራም ጊዜም ቢሆን ባእድ ወንዶች ዘንድ ከሆነች ፊቷን መሰተር ይኖርባታል፡፡

11 አንድ ሰው ኢሕራም ከገባ በኋላ ጠጉሩንም ሆነ ጥፍሩን መቁረጥ አይፈቀድለትም፡፡ እንዲሁም ምንም ዓይነት ሽቱ መንካት የለበትም፡፡

12 ለሐጅ ወይም ለኡምራ ሥራ ወደ መካ ለመግባት ያሰበ ሰው ሳይሐርም

ሚቃቱን«የኢህራም ቦታን» ማለፍ አይፈቀድለትም፡፡

13 ህግ የሚፈቅዳቸው የሀጅና ኡምራ ሥራ ዘዴዎች ሦስት ዓይነት ናቸው፡፡ እነሱም ተመቱእ፣ ቂራንና ኢፍራድ ይባላሉ፡፡ ከነሱም በላጩ ተመቱእ ነው፡፡

- በተመቱእ መሐረም ካሰበህ ኡምራን በመነየት«በማሰብ» "ለበይክ አላሁመ ኡምረተን" ትላለህ፡፡

- በቂራን መሐረም ከፈለግህ ኡምራንና ሐጅን በመነየት "ለበይክ አላሁመ ኡምረትን ወሐጀን" ትላለህ፡፡

- በኢፍራድ መሐረም ከፈለግህ ደግሞ ሐጅን በመነየት "ለበይክ አላሁም ሐጀን" ትላለህ፡፡

14 **በሐጅና በኡምራ የሚሐረም ሰው በሽታና የመሳሰሉ ነገሮች ሥራውን ባሰበው መልኩ ከመፈጸም የሚያደናቀፉ ነገሮችን ከፈራ ህጉ ቅደመ መንሰፈርት ማስቀመጥን ይፈቅድለታል፡፡ይህውም ከነየተ በኋላ እንዲህ በማለት ነው "የሚያደናቅፍ ነገር ካደናቀፈኝ ከኢሕራሜ የምፈታው በዚያ በተደናቀፍኩበት ቦታ ነው" የዚህ ቅድመ መስፈርት ጥቅሙ እንቅፋት በተፈጠረበት ቦታ ከሐረመው ሥራ መፈታት የሚፈቀደለት መሆኑና ምንም ዓይነት «ህድይም ሆነ ጾም ተለዋጭ» ነገር የሌለበት መሆኑ ነው፡፡**

15 -የሐጅን ሥራ የጀመርክ ወንዲሜ ሆይ! - አላህ ከከለከለህ ሴትን ከመገናኘት፣ ከማመጥ፣ ከክርክርና የፈጣሪን ትእዛት ከመጣስ ታቀብ:: በቃልም ሆነ በተግባር በሙስሊሞች ላይ ጉዳት ከማድረስም ተጠንቀቅ::

16 በሲጋራ ማጨስ ፈተና ውስጥ እንዲሆንክ እንዳይመለስ አድርገህ ለመሰናበት«ለመገላገል» ይህ መልካም አጋጣሚ ነው:: በወንጀል ከመዘፈቅ፣ ገንዘብህን ከማጥፋት፣ ጤናህን ከመጉዳትና ወንዲሞችህን ከማስቸገር ሌላ ጥቅም የማታገኝበት መሆኑን እያውቅህ እስከመቸ ማጨስህን ትቀጥልበታለህ?

17 -አላህ ያሰብከውን ሁሉ ቅን ያደርግልህና- በዚህ ቦታም ሆነ

በሌላው ስፍራ የማስታወሻ ፎቶ እያልክ ጊዜህን ከማባከን ተጠንቀቅ:: በዚህ መሰሉ ቦታ ነብያችን ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም፣ በትክክል እንደተዘገበው “ጌታዬ ሆይ ይዩልኝና ይስሙልኝ የሌለባትን ሐጅ ግጠመኝ” በማለት «ዱኣ ማድረጋቸውን» አስታውስ::

18 -የሐጅን ሥራ የጀመርክ ወንዲሜ ሆይ! - ወደ መካ በምታደርገው ጉዞህ “ለቤክ አላሁመ ለበይክ፣ ለበይክ ላሸሪከ ለከ ለበይክ ኢነልሐምደ ወኒዕመተ ለከ ወልሙልክ ላሸሪከ ለክ” የሚለው ተልቢያ ካፍህ አይለይ::

19 «ከነብያችን የደረሰን» ሱናው ይህን ተልቢያ ለያንዳንድ የሐጅ

ሥራ የያዘ ሰው በግሉ እንዲለው ነው:: በቡዲን የሚባለው ተልቢያ ደግሞ ነብያችን ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ካስተላለፉልን መምሪያ ተካቶ አይገኝም::

20 -የሐጅን ሥራ የጀመርክ ወንዲሜ ሆይ!- «በሚቃቶቹ«የኢሕራም ቦታዎች» አካባቢ ለሐጅ ተሳታፊዎች ንቃት «ትምህርት» የሚሰጥባቸው፣ ሐጅን በተመለከተ መጣጥፎች የሚታደልባቸውና ለአንዳንድ ጥያቄዎች መልስና ማብራሪያ የሚሰጥባቸው ቦታዎች መኖራቸውን ልናስታውስህ እንወዳለን::

አላህ ለእኛም ለናንተም ሃሳብ መቃናትንና ተቀባይነት ማግኘትን

ይችረን፡፡ እንዲሁም ቅንና ትክክለኛውን መንገድ ያሳውቀን፡፡

አላህ የአክብሮታ እዝነቱንና የማክበር ሰላምታውን በንብያችን ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ላይ ያውርድ፡፡

**ኪንግደም ሳውድ ዐረቢያ**
**በእስልምና ጉዳዮች፣ ገንዘብ ስጦታ፣**
**ዳእዋና መምሪያ ሚንስቴር**
**የህትመትና ሳይንሳዊ ምርም**
**ድርጅት**

**መ.ሣ.ቁ**. 61843 **ኮድ** 11478
**ቴሌ**. 00966114736999
**ፋክስ** 00966114737999
**ሪያድ** info@islam.org.sa